# ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም

**ተሻለ ለማ ቱሬ**

ኢትዮጵያ በታሪኳ የመጀመሪያውን አይን ከፋች ምርጫ አካሂዳለች፡፡ በዚህ ምርጫ የህዝብ ይሁንታን ያገኘው ፓርቲ አገሪቱን ለአምስት አመት ለመምራት ስልጣን ይረከባል፡፡ ይህ አዲስ ግን ድንቅ ክስተት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ሲመኙ ብቻ አይደለም ሲሰውለት የነበረው የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ዕውን ሆኗል፡፡ ምንም ተባለ ምን በዘንድሮው ምርጫ ህዝብ አሸናፊ ሆኗል፡፡

ይህን የምርጫ ውጤት ተከትሎ የሁሉም ወገን ራዕይ የተጀመሩ የሠላም የልማት እና ዲሞክራሲ ጥረቶችን በማጠናከር ለዘመናት በረሃብ እና ጦርነት እግር ተወረች የታሰረውን ኢትዮጵያዊ ከዚህ ማለቀቅ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለይም ቅንጅት አካሄዱን ማስተካከል እና የተጠናወተውን የጦርነት አውርድ አባዜ ማረም ይኖርበታል፡፡

ከመጀመሪያው ጀምሮ ተስበው ወደ ውድድር የገቡት ተቃዋሚዎች እኛ ካላሸነፍን ምርጫው ህጋዊ አይደለም በሚለው አቋማቸው ገፍተውበታል፡፡ የቅንጅት መሪ የሆኑት አቶ ኃይሉ ሻውል ከቢቢሲ ሬዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ይህንኑ ውሃ የማይቋጥር አቋም በድጋሚ አንፀባርቀዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የሚሰጡት ምክንያት አዲስ አበባ ውስጥ ከፍተኛውን መቀመጫ ያገኘው ፓርቲ ሌላ ቦታ ማን ሊከላከለው ይችላል ነው የሚሉት፡፡ ለመሆኑ አዲስ አበባ ከኢትዮጵያ ህዝብ 4 በመቶ ብቻ መሆኑን ዘነጉት? አቶ ኃይሉ ሻውል ኢህአዴግ አዲስ አበባ ውስጥ ሳይቀር ማጭበረበሩን ነው የገለፁት፡፡ ለመሆኑ ምርጫው ርዕሰ መዲናዋ ውስጥ ትክክል ነበር ሲሉ ቆይተው ገዢው ፓርቲው አጭበርብሮ አንድ ወንበር አገኘ የሚለው ምክንያት ምን ያህል አሳማኝ ነው ፡፡ ባያጭበረብር ኖሮ እንዷንም አያገኝም ነው?

ለእኔ እንደሚሰማኝ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በገዢው ፓርቲ ወስጥ በነበሩ የማስፈፀም ጉድለቶች ሳቢያ ህብስተመና ነው የወረደላቸው፡፡ አሁን በጥላቻ ያገኙትን ድል አጣጥመው ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ አስተዋጽኦ የማድረግ ፍላጐት ያላቸው ግን አይመስሉም፡፡ እነዚህ ወገኖች ምርጫው ከል ማልበስ ነው አለማቸው፡፡ በግርግር ኢህአዴግን ኢ - ህገመንግስታዊ በሆነ መንገድ ገፍትረን ዘንድሮ ካልጣልን አበቃልን ባይ ናቸው ታቃዋሚዎች መመሪያቸው ዘንድሮ ወይም ይቅር /Now or Never/ የሚል ነው፡፡ እነሱ ስልጣን ይያዙ እንጂ ንፁሃን ቢሞቱ፣ ንብረት ቢወድም፣ዳግም የሽብር ዘመን ቢወለድ ቁባቸው አይደለስም፡፡ አይሞቃቸው፣ አይበርዳቸው፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሌላ አካላቸው አገር ቤት ይሁን እንጂ ጭንቅላታቸው ዋሽንግተን እና ሌሎች የአውሮፓ አገሮች ነው ያለው፡፡ እነዚህ የሰደት ፖለቲካ አራማጆች ደግሞ ኢትዮጵያን የዕልቂት ቁልቁለት ላይ አስቀምጠው መውጣቱን ደጁ በራፍ ሲደፉ ቆይተው ነገሩ ሲከፋ እግሬ አውጪኝ ያሉ የህዝብ ደመኞች ናቸው፡፡ ከነሱ ብሶ የዲሞክራሲን ሀሁ አውሮፓና አሜሪካ ይሰብካሉ፡፡ ለነገሩ ጅብ የማያውቁት አገር ሄዶ አይደል ነገሩ፡፡ አገር ቤት ያሉ የነሱ

ጋሻ ጃግሬዎችም ዲሞክራሲዊ ምርጫን በመጠቀም በዲሞክራሲ ለማጥፋት ታጥቀው ቢነሱም አይሳካላቸውም::

እነዚህ የቀድሞ የደርግ ባለስልጣናት እና ታቃዋሚዎች በውጭ የሚገኙ አንዳንድ ኃይሎች ይህን አላማቸወን ለማሳካት ሥራቸወ ሰልፍ ሆኗል:: ሰልፍ የሚያሰወጡበት መቀስቃሻ ደግሞ ጥላቻ ነው:: ከዚሁ የተለየ አቋም መያዝ ለእነዚህ ወገኖች ክልክል ነው:: ገዢውን ፓርቲ ለማሳቀል የአምባገነን አባዜአቸው አልለቀቀቸውም:: ይሄ ነው ዲሞክራሲ ለነሱ:: የተቃዋሚዎች ሌላው የፕሮፓጋንዳ መሣሪያቸው ውዥንብር ነው:: በውጭ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የተሳሳተ መረጃ ማቅረብ የዕለት ተዕለት ተግባራቸው መሆኑን ለመናገር ነብይ መሆን አያስፈልግም:: ለምሳሌ የቅንጅት አመራር የሆኑት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ቤልጅም ብራስልስ ውስጥ ለደግፊዎቻቸው ባደረጉት ገለጻ 85 በመቶ ህዝብ እንደመረጣቸው በመናገር የተሰብሳቢውን ድጋፍ መሻታቸው ያስፍራል:: ሌላው የቅንጅት አመራር አባል አቶ ይሳሃቅ ክፍሌ ከ29 የሚሊዮን መራጭ 26 ሚሊዮን ቅንጅቱን መርጧል ሲሉ ለቢቢሲ ሲገልፁ ያልተመላሱ ጥያቄዎች ነበሩ:: ዘንድሮ የነበረው የመራጭ ቁጥር 26 ሚሊዮን መሆኑን አያውቁም? ወይስ ከቀጣዩ 4ኛ ምርጫ ተበደሩ?

እኔ የተቃዋሚ ደጋፊዎች አትላንታ ለንደን ወዘተ ሠልፍ ወጡ ሲባል አንድ ነገር ያስቀናኛል:: ሠልፉ ለልማት ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር:: አሜሪካና አውሮፓ ሠላም ወጥተው እየገቡ ለኔና ቢጤዎቼ ጦርነት ይደግሳሉ፣ ዕድሜ ለዲሞክራሲ መንግስት ይሄዳል ይመጣል:: ኢህአዴግ ሌላ አገር ሌላ:: አገር ይቅደም:: ምርጫ የዲሞክራሲ ሂደት አንድ አካል እንጂ ግብ አይደለምና::

የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፋዎች ሌላው አስቂኝ ነገር የዕዳ ሰርዛ አይደረግ የሚለው ቅስቀሳቸው ነው:: በዚህ ረገድ ከተቃዋሚዎች ጋር አንድ አይነት አቋም ያለው የኤርትራ መንግስት ነው:: ለንደን ውስጥ ዓለም ድህነትን እንዲዋጋ የሚንቀሳቀሱት ቦብ ጌልዶፍ እና ማዶና ይህንን ሰምተው ከሆነ ምን ብለው ይሆን ?

ተቃዋሚዎች የጥፋት አባዜ የተጠናውታቸው በመሆናቸው እንጂ ከ4.4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ዕዳ የሚሰረዘው ከ20 -30 ዓመት ባለው ጊዜ ተከፍሎ የሚያልቅ እና ለድሃው ኢትዮጵያዊ የሚውል መሆኑን ዘንግተው አይደለም:: የአሁኑም ምርጫ ኢህአዴግ አሸናፊ ቢባል እንኳ በመጪዎቹ 20 እና 30 ዓመት ዓመታት ተወዳድረው በማሸነፋ የዕዳ ስረዛው ተጠቃሚ የመሆን ፍላጐት የላቸውም እንዴ ? አሳፋሪ ነው:: የአገሬ ሰው ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም ይላል::

ተቃዋሚ ፓርቲዎች የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጠንቆች ናቸው:: ውጭ ባሉ ጋሻ ጀግሬዎቻቸው አማካኝነት ገዢውን ፓርቲ ማስቀል ልማዳቸው ነው:: ከወዲሁ ኢህአዴግን ፍርድ ቤት መገተር ከፈለጉ ህገመንግሥቱን ማስወገድ ከፈለጉ በምርጫ መወዳደርን ምን አመጣው:: ተወደደም ተጠላም ኢህአዴግ የደርግን አምባገነን አስተዳዳር ደም ገብሮ በመገርሰስ በኢትዮጵያ ታስቦ ታልሞ የማይታወቀውን ምርጫ እንዲካሄድ በማድረጉ ቢወደስ ቢሞገስ ያንሰዋል እንጂ አይበዛበትም::